በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የሰ.መ.ቁ 175155

ቀን ጥቅምት 27 2013ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነዓ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

አመልካች፡ በአማጋ ኃ/የተ/የግ/ማህበር ጮራ የጋዝና ኬሚካል ውጤቶች ፋብሪካ - ጠ.ግሩም አየለ ቀረቡ

ተጠሪዎች፡1ኛ. ሂክማ የፈሳሽ ሳሙና ማምረቻ ኃ/የተ/የቡድን ኢንተርፕራይዝ-ጠ. መሀመድ አብደላ ቀረቡ

2ኛ. ኦሽን ኬሚካልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠ. ጌድዮን ወልደዩሀንስ - ቀረቡ

3ኛ. ሚስክ ኢንዱስትሪዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር

4ኛ. ኤች.ሲ.ዜድ አላቂ የጽዳት ዕቃዎች ማምረቻ ኃ/የተ/የግ/ማህበር } አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ139054 በ29/5/11ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 172510 በ26/7/11ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ ቅር በመሰኘት በ07/8/11ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረበ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካች በስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረበው የተሻሻለ ክስ ለክሳሽ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/98 መሰረት ለሁለት አይነት የበረኪና ምርቶች ማለትም ለትልቁ ባለ 800 ሚሊ ሊትር SEDEX እንዲሁም ለትንሹ ባለ 300 ሚሊ ሊትር SEDEX በምዝገባ ቁ.LTM/0189/2005 እና LTOW 0186/2005 በቅደም ተከተል የተመዘገበ እና እስከ 28/10/12ዓ.ም ድረስ

ጸንቶ የሚቆይ የንግድ ምልክት ምዝገባ ሰርተፍኬት ከኢትዮጵያ አእምሮአዊ ንብረት ጽ/ቤት በ2005ዓ.ም የተሰጠ ሲሆን የንግድ ምልክቶቹ የተመዘገቡት እና ፈቃድ የተሰጠው በቃል እና በስእል(በቅርጽ) (በምስል) ከመሆኑም ባሻገር የቀለም አይነቱ በአዋጁ አንቀጽ 5(2) መሰረት ጥቁር እና ነጭ ነው። የንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ አላማው የተለያዩ እቃዎችን በማምረትና በማከፋፈል ወይም አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መልካም ስም እና ዝና ለመጠበቅ እንዲሁም በተመሳሳይ ስራዎች እና አገልግሎቶች መካከል ማሳከርን ለማስወገድ እና አንድን ምርት/እቃ ወይም አገልግሎት በቀላሉ ለመለየትና የንግድ ምልክቱ በአገልግሎት ተጠቃሚው (ኮንሲዩመሩ) ላይ ግርታ እንዳይፈጥር ለማድረግ ነው።

የንግድ ምልክቱ ጮራ የጋዝና ኬሚካል ውጤቶች ማምረቻ ፋብሪካ በመንግስት እጅ ከነበረበት ግዜ ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ሲሆን ድርጅቱ በአመልካች ስም ከተዛወረበት ከ2001ዓ.ም ጀምሮ የንግድ ምልክቶቹ በየግዜው እየታደሱለት በባለቤትነት እየጠቀመበት ሲሆን ለተጨማሪ 7 አመታት ከ2005ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2012ዓ.ም ድረስ ታድሶለታል። አመልካች ምርቶቹን ለማስተዋወቅ በተለያዩ ግዜያት የማስታወቂያ ስራ ለመስራት ከፍተኛ ገንዘብ አውጥቷል። ነገር ግን አራቱም ተጠሪዎች የንግድ ምልክት ምዝገባ የተሰጣቸው በእቃ(በስም) ብቻ ሆኖ እያለ አመልካችን ሳያስፈቅዱ 1ኛ ተጠሪ የአመልካችን የተመዘገበ ቅርጽ እንዳለ በመጠቀም ስሙን ብቻ SMART በሚል በመቀየር በአመልካች ስም የተመዘገበውን የንግድ ምልክት በመጠቀሙ፤ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ስም የተመዘገበው እና ፈቃድ የተሰጠበትን ቅርጽ(ስዕል) እንዳለ በመጠቀም ስሙን ብቻ BRAVO በሚል ቃል በመቀየር የአመልካችን የንግድ ምልክት በመጠቀሙ፤ 3ኛ ተጠሪ በአመልካች ስም የተመዘገበውንና ፈቃድ የተሰጠበትን ቅርጽ(ስዕል) እንዳለ በመጠቀም ስሙን ብቻ BRAVO በሚል ቃል በመቀየር የአመልካችን የንግድ ምልክት በመጠቀሙ፤ 4ኛ ተጠሪ በአመልካች ስም የተመዘገበውንና ፈቃድ የተሰጠበትን ቅርጽ(ስዕል) እንዳለ በመጠቀም ስሙን ብቻ TSEDAL በሚል ስም በመቀየር የአመልካችን የንግድ ምልክት ተጠቅሟል። ተጠሪዎች የአመልካችን የንግድ ምልክት በመጠቀማቸው እና ምርቱም ደረጃውን ያልጠበቀ በመሆኑ የአመልካችን ስም እና ዝና ከማጉደፋም በላይ በአመልካች ላይ ከፍተኛ ኪሳራ አድርሷል። ምንም እንኳን በአመልካች ላይ ኪሳራ የደረሰው የንግድ ምልክቱ ባለቤትነት በአመልካች ስም ከተዛወረበት ግዜ ጀምሮ ቢሆንም በተለይ በ2007 በትልቁ ባለ 800 ሚ.ሊ. ሊትር SEDEX ላይ የብር 4,120,000(አራት ሚሊዮን አንድ መቶ ሀያ ሺህ ብር) እንዲሁም ባለ 300 ሚ.ሊ. ሊትር SEDEX ላይ የብር 2,090,379.55( ሁለት ሚሊዮን ዘጠና ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ዘጠኝ ብር ከሀምሳ አምስት ሳንቲም) በድምሩ የብር 6,270,379.55 ኪሳራ ደርሷል። ስለሆነም ተጠሪዎች የአመልካችን የንግድ ምልክት በመጠቀም ምንም አይነት ምርት እንዳያመርቱ እና የአመልካችን ምልክት በመጠቀም ምንም አይነት የበረኪና ምርት እንዳያመርቱ እና እንዳያሰራጩ፤ በአመልካች ላይ ለደረሰው ኪሳራ ብር 6,210,379.55 ከ9% ወለድ ጋር ወጪና ኪሳራን ጨምሮ ለአመልካች እንዲፍሉኝ እንዲወሰንልኝ በማለት ዳኝነት የጠየቀ ሲሆን የሰነድ እና እና የሰው ማስረጃዎችን አቅርቦ፤ ምስክሮች ቆጥሮ፤ የሰነድ ማስረጃ በፍ/ቤቱ ትእዛዝ እንዲቀርብለት ጠይቋል።

1ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ አመልካች የንግድ ምልክት በሚል ክስ ያቀረቡበት በበረኪና እቃነት የሚታወቅና በንግድ ምልክትነት ሊያዝ የማይገባ የበረኪና ምርት ወደ አገራችን ከውጭ ሀገር ይገባ ከነበረበት ግዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ አመልካች የንግድ ምልክት ነው በሚሉት እቃ እና ቅርጽ ይገባ የነበረ በመሆኑ ለከሳሽ መብት የሚያስገኝ ሊሆን የማይገባ ሲሆን፤ በንግድ ምልክት ምዝገባና ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 501/96 አንቀጽ 6 መሰረት ይህ በረኪና የሚለው በጋራ መግባቢያነት የሚያገለግል ሲሆን ሁሉም አምራቾች የራሳቸውን ምርት ለመለየት በማሸጊያ ላይ የራሳቸው የንግድ ስም የሚጻፍ ሲሆን የበረኪና ማሸጊያን በብቸኝነት ካልተቆጣጠርኩ የሚለው ከአዋጁ መንፈስ ውጪ ነው፤ አመልካች በንግድ ምልክትነት የተሰጣቸው የንግድ ምልክት አይነት የቃል እና የስእል እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 2(12) ከተዘረዘሩት ውስጥ "የእቃ መያዣ" ወይም የመያዣዎቻቸውን ቅርጽ የማያካትት ስለሆነ አመልካች ያቀረቡት ክስ በህግ ከተሰጣቸው የንግድ ምልክት አይነት ውጪ የበረኪና መያዣ እቃ "ቅርጽ" በማካተት ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤ 1ኛ ተጠሪ አመልካች በንግድ ምልክትነት ያስቀመጡት ሴዴክስ (SEDEX) ወይም ሴዴ( SEDE) የመያዣ ስዕሉን በንግድ ምልክትነት አልተጠቀምኩም፤ 1ኛ ተጠሪ የተጠቀምኩት SMART የሚለው ቃል አመልካች ከሚጠቀሙበት ቃል ጋር ፈጽሞ የማይገናኝ ስለሆነ ለተገልጋይ ምንም አይነት ማሳከር እንዳይፈጥር 1ኛ ተጠሪ የምጠቀምበት የበረኪና ምርት ማሸጊያ ከአመልካች ማሸጊያ የሚለይ ሲሆን ይኸውም አመልካች የምጠቀምበት ማሸጊያ አናቱ ላይ ክብ ማንጠልጠያ ጆሮ የሌለው ሲሆን በተገልጋዮች እንኳ ጆሮ የሌለው ተብሎ ተለይቶ የሚታወቅ በመሆኑ እና መሰረታዊ የቅርጽ ልዩነት ስለሆነ ተገልጋዮችን ያምታታል ሊባል አይችልም። ለአመልካች የንግድ ምልክት ከተሰጠበት ግዜ አንጻር ደረሰብኝ የሚለው ኪሳራ እጅግ የተጋነነ ነው፤ 1ኛ ተጠሪ ገና በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ የተደራጀ ከመሆኑና ምርቱን ቤት ለቤት በየሱቁ እያስተዋወቀ ያለ በመሆኑ በአመልካች ላይ ይህን ያህል ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ስለማይገመት ኪሳራ ክፈል ሊባል አይገባም፤ በአዋጁ አንቀጽ 41 መሰረት 1ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ሆነ ብዬ የጣስኩባቸው የንግድ ምልክት የሌለ በመሆኑና በማስረጃም ያላስረዱ በመሆኑ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቆ የሰነድ እና የሰው ማስረጃዎችን አቅርቧል።

2ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ በብይን ውድቅ ከተደረገ ሲሆን በፍሬጉዳዩ ላይ ባቀረበው መልስ 2ኛ ተጠሪ ለሚያመርተው በረኪና ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ20/12/11ዓ.ም አመልክቶ በ17/11/07ዓ.ም "ብራሽ" የሚል የንግድ ምልክት በተሰጠው መሰረት የማንንም የንግድ ምልክት አልጣሰም፤ በዚህ የንግድ ምልክት የተሳከረ ተግባር አልፈጸመም፤ አመልካች ካሳ እንዲከፈለው አመለከተ እንጂ ደረሰብኝ የሚለው ጉዳት ከመቼ እስከ መቼ እንደደረሰበት እና በማን እንደደረሰበት አላሳየም፤ 2ኛ ተጠሪ በአመልካች ላይ ያደረሰው ጉዳት የለም፤ ለ2ኛ ተጠሪ የተሰጠው የንግድ ምልክት የሚሰረዝበት ምክንያት የለም እንጂ አለ ቢባል እንኳ በመጀመሪያ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ማመልከቻ ሊቀርብ እና የጽ/ቤቱ ምላሽ አሉታዊ የሆነበት አመልካች ጉዳዩን ለፍ/ቤት ማቅረብ እንደሚችል በአ/ቁ 501/96 ላይ የተመለከተ በመሆኑ አመልካች ጉዳዩን ማቅረብ ያለበት ለጽ/ቤቱ እንጂ ለዚህ ፍ/ቤት አይደለም፤ ወጪዎችን በተመለከተ አመልካች ለ2ኛ ተጠሪ የሰጠው ማስጠንቀቂያ በሌለበት ሁኔታ

ሃለፊነት የለብኝም፡፡ ስለሆነም ክሱ ከወጪና ኪሳራ ጋር ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቆ የሰነድ እና የሰው ምስክሮች ቆጥሯል፡፡

3ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ተጠርቶ ባለመቅረቡ በሌለበት ክርክሩ እንዲቀጥል ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን፤ 4ኛ ተጠሪ ባቀረበው መልስ ለ4ኛ ተጠሪ በሰርተፍኬት ቁ. 4748 በ2001ዓ.ም ለጸዳለ በረኪና ምርት ሽያጭ የሚያገልግል በረኪና በሚል ስም በአንቀጽ 31 መሰረት የንግድ ምልክት የተሰጠው ሲሆን በአ/ቁ 501/98 መግቢያ ላይ ከተደነገገው አንጻር በአመልካች በረኪና ትልቁ SEDEX ትንሹ ሴዴ (SEDE) በሚል የተጻፈበት ሲሆን በ4ኛ ተጠሪ ምርት ላይ በቃል ጸዳል በረኪና የሚል የንግድ ምልክት የተጻፈበት ሲሆን የአመልካች የቀለም ቅንጅት በንግድ ምልክቱ ላይ የተገለጸው ጥቁርና ነጭ ሲሆን የአመልካች ግን ቢጫ ቀለም በመሆኑ የንግድ ምልክቶቹ ፈጽሞ የማይመሳሰሉ በመሆናቸው አመልካች የሚያሳስት እና የሚያሳክር በማለት ያቀረበው ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች 4ኛ ተጠሪ የንግድ ምልክትን በመጠቀሙ ደረሰብኝ ያለውን የኢኮኖሚ ጉዳትና ኪሳራ ከማስቀመጥ ባለፈ ይህ ጉዳት በእርግጥ ስለመድረሱ ያቀረበው ማስረጃ ስለሌለ ክሱ ከወጪና ኪሳራ ጋር ውድቅ እንዲደረግ በማለት ጠይቆ የሰነድ ማስረጃ አቅርቧል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን በቃል ካከራከረ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ አመልካች አምርቶ ለገበያ ለሚያቀርበው የበረኪና ምርት የሚጠቀምበት የንግድ ምልክት ሀምሌ 12/2005ዓ.ም ቁጥሩ LTM/0186/2005 በሆነ ሰርተፍኬት በጽ/ቤቱ የተመዘገበ በመሆኑ በሰርተፍኬቱ ላይ የንግድ ምልክት አይነት የቃል እና የምስል (word and logo) በሚል መገለጹ የጥበቃው ወሰን የበረኪና መያዣውን እቃ በተመለከተ ስለሚኖረው የመብት ሁኔታ እንዲገልጽ፤ የንግድ ምልክቱ የበረኪና መያዣውንም የሚጨምር ስለመሆኑ፤ የበረኪና መያዣ ለንግድ ምልክትነት እንዲመዘገብላቸው የጠየቁ ካሉ ተጣርቶ ጭምር እንዲቀርብ ለኢፌዲሪ የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ20/10/10ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቶ ጽ/ቤቱም በ19/11/10ዓ.ም ለፍ/ቤቱ በሰጠው መልስ በአ/ቁ 501/98 አንቀጽ 2(12) መሰረት የንግድ ምልክቶች ምዝገባ እንደሚሰጥ በዚሁ መነሻነት ለአመልካች የተሰጠው የንግድ ምልክት የቃልና የምስል የሚል መሆኑን፤ይህም ጥበቃ የሚያገኙት በተመዘገበው ቃልና በሚታየው ምስል ላይ መሆኑን፤ይህም ከባለ 3 ማእዘን ገጽታ መብት የሚለይ እና የንግድ ምልክቱ የበረኪና መያዣውን እንደማይጨምር በመግለጽ፤ የበረኪና መያዣውን ለንግድ ምልክትነት እንደሚዘገብላቸው የጠየቁ ሰዎች ስለመኖራቸው ሆነ ጥያቄው ውድቅ ስለመደረጉ መረጃ እንዳላገኘ ገልጿል፡፡

ከዚሁ ሂደት በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪዎች የአመልካችን የንግድ ምልክት መብት ጥሰዋል ወይንስ አልጣሱም? በአመልካች ላይ የደረሰ የንግድ ገቢ ኪሳራ አለ የለም? ተጠሪዎች ኪሳራ ሊከፍሉ ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚሉትን ነጥቦች በጭብጥነት በመያዝ ጉዳዩን መርምሮ የንግድ ምልክቶች ምዝገባ አዋጅ ቁ.501/98 አንቀጽ 4 የንግድ ምልክት ባለቤትነት መብት የሚገኘውና በ3ኛ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው የንግድ ምልክት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሰጥ እንደሆነ ከደነገገው አንጻር አመልካች የንግድ ምልክቱን ያስመዘገበው፤ የምስክር ወረቀት የወሰደበት ምንድን ነው የሚለው ሲታይ የአዋጁ አንቀጽ 2(12) ለንግድ ምልክት የሰጠውን ትርጉም በመዘርዘር በተያዘው ጉዳይ የአመልካች የንግድ ምልክት ቃል እና ምስል መሆኑን የቀረበው

የምዝገባ ሰርተፍኬት ያስገነዝባል፤ ይህም ማለት ቃሉ SEDEX ወይም SEDE የሚል ሲሆን ምስሉ ደግሞ የበረኪና መያዣ እቃ የሚመስል ስእል ነው፤ ይህ ስእል ወይም ምስል ከአዋጁ አንቀጽ 2(12) አኳያ ወደ በረኪና እቃ የሚሸጋገር እና የእቃው ቅርጽ ላይ መብት የሚያሰጥ አይደለም፤ ስለሆነም አመልካች የንግድ ምልክት ቅርጽ(መያዣው) ላይ የወሰዱት የምስክር ወረቀት የሌለና በ3ኛ ወገን ላይ የመብት ጥያቄ ማንሳት የማይችሉ መሆኑን የሚስረዳ በመሆኑ ተጠሪዎች የበረኪና መያዣ እቃ ቅርጹን መጠቀማቸው የአመልካችን የንግድ ምልክት ተጠቀሙ የሚያስብል ሆኖ አልተገኘም፤ አመልካችም መብት ባላገኘበት ነገር ላይ ክስ ያቀረበ ስለሆነ በማለት ክሱን ውድቅ በማድረግ እንዲሁም ተጠሪዎች የሚከፍሉት የኪሳራ ገንዘብ የለም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ የተገለጹትን ውሳኔ እና ትእዛዝ በመቃወም ሲሆን ይዘቱም ለአመልካች የንግድ ምልክት የተሰጠው እና የንግድ ምልክቱም የተመዘገበው በስምና በቅርጽ ሲሆን ይህ በንግድ ምልክት ምዝገባው ሰርተፍኬት ላይ የሚገኘው ምስል የበረኪና መያዣው ቅርጽ ነው፡፡ የበረኪና መያዣው ቅርጽ በምስል ሲቀመጥ ሊሆን የሚችለው በሰርተፍኬቱ ላይ የሚገኘው ምስል ነው፤ በምስልም ሊቀመጥ የሚችለው የበረኪና መያዣው ቅርጽ ነው፤ የበረኪና መያዣው ቅርጽ ሳይኖር ስለምስል ለመናገር የማይቻል ሆኖ ሳለ የስር የከፍተኛው ፍ/ቤት ለአመልካች የተሰጠው የንግድ ምልክት በቃልና በምስል መሆኑን ተቀብሎ ነገር ግን የአ/ቁ 501/98 አንቀጽ 2(12)ን ድንጋጌን በአግባቡ ባለመረዳት ቅርጹ ወይም ምስሉ ወደ በረኪና መያዣ እቃ የሚሸጋገር እና የእቃው ቅርጽ ላይ መብት የሚያሰጥ አይደለም፤ የአመልካች የንግድ ምልክት መያዣውን ወይም ቅርጹን የሚጨምር አይደለም ሲል የሰጠው ውሳኔ አግባብ አይደለም፡፡ በኢፌዲሪ ህገመንግስት አንቀጽ 79(3) መሰረት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሰጡ የሚገባው ህግን መሰረት አድርገው ሆኖ ሳለ፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መቁ 36848 በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊሰጡ የሚገባው የቀረበውን ክርክር፤ ማስረጃ እና ህግን መሰረት በማድረግ ሆኖ ሳለ አመልካች በኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በኩል በቃልና በቅርጽ በምስል የተሰጠውን የንግድ ምልክት አቅርቦ ሳለ የከፍተኛው ፍ/ቤት ሰበር በሰጠው የህግ ትርጉም መሰረት የቀረበውን ማስረጃና ህግን መሰረት አድርጎ መወሰን የነበረበት በመሆኑ የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት እና የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ውሳኔዎች ተሽረው ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት የተጠየቀውን ኪሳራ በአንድነት እና በነጠላ እንዲከፍሉ፤ በአመልካች ስም የተመዘገበውን የንግድ ምልክት በአዋጁ አንቀጽ 40 መሰረት እንዳይጠቀሙ፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ይህ አቤታቸው ተመርምሮ ለአመልካች የንግድ ምልክቱ በስምና በቅርጽ የተሰጣቸው መሆኑ ያለከራከረ ጉዳይ ከሆነ ቅርጹ የበረኪና መያዣውን የሚጨምር አይደለም፤ ምክንያቱም ቅርጹ ባለ 3 ማዕዘን ቅርጽ ያለው ሊሆን ይገባል በሚል የተሰጠውን ዳኝነት አግባብነት ከአ/ቁ 501/1998 አንቀጽ 2(12) አንጻር ለማየት

እንዲቻል ለሰበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ12/9/11ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 1ኛ ተጠሪ በ18/11/11ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ ለአመልካች በአ/ቁ 501/96 አንቀጽ 2(12) መሰረት በግልጽ የቃል እና ምስልን የሚያካትት ሰርተፍኬት ተሰጥቶት እያለ፤ ለጽ/ቤቱ ጥያቄ አቅርቦ የበረኪና መያዣ ቅርጽን የሚያካትት ሰርተፍኬት ባልተሰጠው ሁኔታ፤ በአዋጁና በጽ/ቤቱ መመሪያ መሰረትም ጥሰት ተፈጽሞበት ከሆነ እንዲጣራ ለጽ/ቤቱ ባላቀረበበት ሁኔታ፤ ተጠሪዎች መብቱን ሳንነካ ክልከላ ይደረግባቸው ሲል ያቀረበው አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ፤ አመልካች በማን ምን ያህል ኪሳራ እንደደረሰበት ማስረጃ ባላቀረበበት ሁኔታ፤ የስር ፍ/ቤትም በዚህ ረገድ አከራክሮ፤ ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ባልሰጠበት ሁኔታ ኪሳራ ይከፈለኝ ሲል ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት ስለሌለው ውድቅ እንዲደረግ፤ የስር ፍ/ቤቶች በየደረጃው የሰጡት ውሳኔ የህግ ስህተት የሌለው በመሆኑ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪ በ18/11/11/ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ ለአመልካች የተሰጠው የንግድ ምልክት ቅርጽን የሚጨምር አለመሆኑ በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ በመሆኑ፤ አመልካች ይከፈለኝ በማለት የጠየቀው የካሳ ክፍያ በምን አግባብ እንዴት በምን ያህል ማን መክፈል እንዳለበት ያቀረበው የሰበር አቤቱታ የለም፤ ስለሆነም የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና በማለት ጠይቋል፡፡

3ኛ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ተደርጎለት ሳይቀርብ የቀረ በመሆኑ ችሎቱ በ28/1/11ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የ3ኛ ተጠሪን የጽሁፍ መልስ የመስጠት መብቱን አልፎታል፡፡

4ኛ ተጠሪ በ19/10/11ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ በአመልካች ስም የተመዘገበው የንግድ ምልክት የእቃ መያዣው ቅርጽ ላይ መብት የማያሰጥ በመሆኑ፤ አመልካች በ4ኛ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበት ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ አቤቱታው ውድቅ ተደርጎ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ አመልካች እንዲከፍለኝ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች በ27/1/12ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ፤ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ እና ትእዛዝ አግባብነት እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

አመልካች በሰበር አቤቱታው ለአመልካች ባለ 800 ሚሊ ሊትር ሴዴክስ በረኪና እና ባለ 300 ሚሊ ሊትር ሴዴክስ በረኪና የንግድ ምልክት የተሰጠው በስምና በምስል(በቅርጽ) ነው፤ በንግድ ምልክት ምዝገባው ሰርተፍኬት ላይ የሚገኘው ምስልም የበረኪና መያዣው ቅርጽ ነው ሲል የተከራከረ ሲሆን፤ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ግራቀኙ በቃል ሊከራከሩበት ይገባል ያለውን ነጥብ በመለየት ግራቀኙ እንዲቀርቡ በ29/8/12ዓ.ም እና በ22/11/12ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቶ መስከረም 27 ቀን 2013ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች እና 1ኛ ተጠሪ ቀርበው ባደረገው ማጣራት አመልካች ለተጠሪዎች የተሰጣቸውን የንግድ ምልክት እንደማይቃወም የገለጸ ሲሆን፤ ማስረጃዎችን የመስማት፤ የመመርመር እና የመመዘን ስልጣን ያለው የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ለገበያ ለሚያቀርበው የበረኪና ምርት የተሰጠው የንግድ

ምልክት የበረኪና መያዣውን ዕቃ ጭምር የሚጨምር ስለመሆኑ አጣርቶ ማብራሪያ እንዲያቀርብ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት በ20/10/10ዓ.ም ለሰጠው ትእዛዝ ጽ/ቤቱ ለአመልካች የተሰጠው የንግድ ምልክት የበረኪና መያዣውን እንደማይጨምር በ19/11/10ዓ.ም ከሰጠው ምላሽ በፍሬነገር ደረጃ ስለማረጋገጡ የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ውሳኔ ይዘት የሚያስረዳ ሲሆን ይህ ከሆነ ደግሞ የስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት አመልካች በበረኪና መያዣ እቃ ቅርጽ ላይ የወሰደው የምስክር ወረቀት ባለመኖሩ፤ ለአመልካች በቃል እና በምስል የተሰጠው የንግድ ምልክት የበረኪና መያዣ እቃው ላይ መብት የሚያሰጥ አይደለም፤ ተጠሪዎች የበረኪና መያዣ ቅርጹን መጠቀማቸው የአመልካችን የንግድ ምልክት ተጠቀሙ አያስብልም በማለት ድምዳሜ ላይ በመድረስ አመልካች መብት ባላገኘበት ነገር ላይ ያቀረበው ክስ ነው በማለት የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ በሙሉ ውድቅ በማድረግ ውሳኔ መስጠቱን፤ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የስር የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሰጠው ትእዛዝ ይግባኙን መሰረዙን ይህ የሰበር ችሎት የሚነቀፍ ሆኖ አላገኘውም፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ139054 በ29/5/11ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 172510 በ26/7/11ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል፡፡
2. በዚህ የሰበር ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. ይህ የሰበር ችሎት በዚህ መዝገብ በ15/9/11ዓ.ም በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 234871 የተጀመረው አፈጻጸም ታግዶ እንዲቆይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለስር የፌ/ከ/ፍ/ቤት ይጻፍ፡፡
4. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍርድ ቤቶች ይድረስ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሶስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ጥ